# 2024 - 2025 የትምህርት ዓመት የቅድመ መዋእለ ህፃናት/ሄድስታርት ፕሮግራሞች መቅረብ ያለባቸው ሠነዶች ዝርዝር

Division of Early Childhood, Title I Programs and Recovery Funds
Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Room 143, Rockville, Maryland 20852

ለቅድመ መዋእለ ህፃናት/ሄድስታርት ልጆች፣ (የአካል ጉዳተኝነት ያላቸውን ህጻናት ጨምሮ) የማመልከቻ ቅጽ ይዘው ያለቀጠሮ ከሰኞ እስከ ዓርብ 9:00 a.m. እስከ 4:00 p.m. = Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Rockville, Maryland, 20852 በአካል መቅረብ ይችላሉ። እንዲሁም፣ማመልከቻዎችን በ ParentVue ወይም www.montgomeryschoolsmd.org ማቅረብ ይቻላል። ለበለጠ መረጃ፡ 240-740-4530 ይደውሉ።

**ማመልከቻውን ለመሙላት፣ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሠነዶች ማቅረብ አለብዎት።**

የሚከተለውን ዝርዝር በመመሪያነት ይጠቀሙ፡-

❑ 1. የተማሪ የእድሜ ማረጋገጫ እና መታወቂያ— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች አንዱን ያቅርቡ።
- የልደት ሠርተፊኬት
- ፓስፖርት
- የሃኪም ሠርተፊኬት
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት
- የሆስፒታል ሠርተፊኬት
- የሠነድ ማረጋገጫ/ኖቶራይዝ የተደረገ የወላጅ ቃለመኃላ/affidavit
- የልደት ምዝገባ ሠርተፊኬት፣ ወይም
- ሌሎች ህጋዊ የሆኑ ወይም የሠነድ ማረጋገጫ/ኖቶራይዝ የተደረጉ የልጆች መታወቂያ እና የልደት ቀን ማረጋገጫ።

❑ 2. ተማሪው(ዋ)ን ወደ ትምህርት ቤት የሚያስገባው/የምታስገባው ሰው መታወቂያ እና ከተማሪው(ዋ) ጋር ያለ ግንኙነት—
ፎተግራፍ ያለበት የማንነት መታወቂያ ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው—እባክዎ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች አንዱን ያቅርቡ።
- የመንጃ ፈቃድ
- ፓስፖርት
- ከሞተር ተሽከርካሪ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የሚሰጥ መለያ/መታወቂያ ካርድ
- ሌላ ____________________

ከተማሪ ጋር ያለ ግንኙነትን በሚመለከት የሚካተቱ ምሣሌዎች—ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች አንዱን ያቅርቡ።
- የልጅ የልደት ሠርተፊኬት
- የፍርድ ቤት ትዕዛዝ
- ለመለያየት የተደረገ ስምምነት ወይም የፍቺ ሠነድ፣ ወይም
- ሌላ ህጋዊ መታወቂያ ____________________

❑ 3. የቤተሰብ የገቢ ማረጋገጫ (ጎልማሳ የቤተሰብ አባላት በሙሉ)— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት እርስዎን የሚመለከቱ ሠነዶችን በሙሉ ያቅርቡ።
ምሳሌዎች የሚያካትቱት፡-
- Tax return for 2023—1040, W2s, Schedule C/1099
- ሦስት ወቅታዊ የደሞዝ (ቼክ) ክፍያ ሠነዶች/pay stubs
- የሥራ ቅጥር ደብዳቤዎች
- ስለ ልጅ ማሳደጊያ ድጋፍ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ደብዳቤ
- የዶላር መጠን የሚያሳይ የፋይናንስ እርዳታ ደብዳቤ
- ጊዜያዊ የገንዘብ ድጎማ (TCA)
- የኪራይ ገቢ ደብዳቤዎች
- የሥራ አጥነት፣ የአካል ስንክልና ገቢ፣ ወዘተ

❑ 4. ወቅታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት ማስረጃ
- የግል መኖሪያ ቤት ባለቤት ከሆኑ —ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ ነው
- ቤትዎ የተከራዩት ከሆነ—ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ ሊዝ ነው* (የሚመለከትዎ ከሆነ፣ የ HOC፣ የኪራይ ወይም ዩቲሊቲ ድጋፍ የሚሰጥ ካለ አባሪ ይደረግ)።
  *ኦርጅናል የሊዝ ስምምነት ያበቃለት ከሆነ፣ የሊዙን ቅጂ እና ወቅታዊ ዩቲሊቲ ቢል ያቅርቡ
- በ MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ በህጋዊነት ኗሪ ከሆነ/ች የቤት ባለቤት ጋር ወይም ከተከራይ ጋር በደባልነት የሚኖሩ ከሆነ—
- የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም/ኖቶራይዝ የተደረገ MCPS Form 335-74፣የመኖሪያ ቤት ደባልነት መግለጫ/Shared Housing Disclosure በአግባብ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፣ የቤት ባለቤትነት ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ/ቢል ቅጂ፣ ወይም የመኖሪያ ቤት ኪራይ-ሊዝ ቅጂ (ኦርጅናል የኪራይ ውል/ሊዝ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፣ የሊዝ ውል ቅጂ እና ዩቲሊቲ ክፍያ ሠነድ-ቢል)፣ ተፈርሞበት ኖቶራይዝ የተደረገ የ MCPS Form 335-74፣ እና ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቁነት ያለው/ያላት ተማሪ በተገለጸው አድራሻ ነዋሪ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሦስት ሠነዶችን ማቅረብ ያስፈልጋል። MCPS Form 335-74 ተሞልቶ እና ተፈርሞበት ህጋዊ ሰነድ መሆኑ የተረጋገጠ/notarized ከሆነ አድራሻ ለማረጋገጥ ከሦስቱ አስፈላጊ ማረጋገጫዎች አንዱ ሊሆን ይችላል።

❑ 5. እባክዎ የእርስዎን ሁኔታ የሚመለከት ከሆነ የሚከተሉትን ሠነዶች ያቅርቡ፡-
- የህጻኑ(ኗ) የህክምና ኢንሹራንስ ካርድ (ካለ)
- WIC Folder-ፋይል (የሚመለከትዎት ከሆነ)
- የምግብ ድጎማ ፕሮግራም/Food Supplement Program (FSP) ደብዳቤ (ቀደም ሲል ፉድ ስታምፕ ይባል ነበር) (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- የልጅ እንክብካቤ ድጎማ ቫውቸር (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- የልጅ እንክብካቤ ሰጪ ስም እና አድራሻ (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- በልጁ/በልጅቱ ግላዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም/Individualized Education Program (IEP)፣ የሞግዚትነት ማረጋገጫ (የሚመለከትዎ ከሆነ)